# እምቢ አላረጅም ?

( ዓለሙ አሎ )

ጠጅ ቤት ስጋው ቤት ፈላጬ ቆራጬ
ሽማግሌው ሆንዋል ዘንድሮ በጥባጬ።

እኛው ወልደናቸው እኛኑ ያማሉ
ሽማግሌው ሁሉ ምን ነካው እያሉ።
ይበለን ይበለን ማንም ይዘርጥጠን
በገዛ እጃችን አናረጅም ብለን።

ከማስታረቅ ይልቅ ሰው እናጋጫለን
ለግዜርም ለርጅናም እጅ አንሰጥም ብለን።
ከኛ እሚጠበቀው ሰላም ፍቅር ማንገስ
አይደለም ማጫረስ ማባላት ማናከስ።

በርጅና ዘመኑ ነገር አቀጣጣይ
ያራል ይበግናታል በምድርም በሰማይ።
ሾተላይ ደብተራ ጳጳሱም ወዮለት
እዚህ ይቃጠላል እዛም አይቀርለት።

ለኛም ሆነ ለሰው ላገርም አይበጅም
አንድ ፍሬ ልጅ ነኝ እምቢኝ አላረጅም።
ሁለቱ ለየቅል መሆንና መምሰል
እንደ ልጅ ስላሰብን ልጅ ነን ማለት አይደል።
አላረጀሁም ቢል አይመስልም ወይ ጉራ
የኛ አይነት ደካማ በሰው የሚመራ።

ሰው ለመሸምገሉ ዋና ምልክቱ
ነገር ማበላሸት ከመስመር መውጣቱ
ሆደ ባሻነቱ መዘንጋት መርሳቱ
እሹሩሩ አድርጉኝ እዘሉኝ ማለቱ።

ሰው ከሸመገለ ጥርሱን ካስነቀለ
ጆሮው ካላጣራ ድምጹ ከሰለለ
አይኑ ከደከመ ጉልበቱ ከዛለ
በዊል ቸር ከሄደ አልጋ ላይ ከዋለ
በክብር ስልጣኑን ቢያስረክብ ምን አለ።

መድረኩን እንተው ለወጣት ለልጁ
ካረጁ ካፈጁ ከጃጁ አይበጁ።
ከታሪክ እንማር ቦታውን እንልቀቅ
ልክ እንደ ንጉሱ ተገፍትረን ሳንወድቅ።

የሚስማማው ቦታ ላዛውንቶች ሕይወት
ቤተ ክርስቲያን ነው አሊያም መሽታ ቤት።

www.quatero.net © 2000 - 2007 all rights are reserved

www.quatero.net © 2000 - 2007 all rights are reserved